የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)

የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት (Family Life Education)፣ 6ተኛ ክፍል ውስጥ

ዳግም-ምልከታ ለማድረግ ያለ-መብት: ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ በትምህርት ቤት ክፍሉ/division የሚሰጠውን፤ በፕሮግራሙ ውስጥ ጥቅም-ላይ የሚውለውን የጽሁፍ እና የድምፅ-እይታ (audio-visual) ትምህርትን ቁሳቁሶችን ጨምሮ፤ የ'Family Life Education Program'ን በድጋሚ-የመመልከት መብት አላቸው። ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ ልጃቸውን ከ'Family Life Education' የትምህርት-አሰጣጥ፣ ከሁሉም ወይም ከተወሰነው-ከዚህ ክፍል እንዲወጡ-ፈቃድ እንዲያገኙ የማድረግ መብት-አላቸው።

የፕሮግራም ግቦች: የACPS፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፤ ሁሉን-አቀፍ የሆነ፣ ቅደም-ተከተል ያለው ከK-12 ፕሮግራም ሆኖ፤ በቤተሰብ አኗኗር እና በማህበረሰ ግንኙነቶች ላይ - ለዕድሜያቸው-ተገቢ በሆነ የትምህርት-አሰጣጥን አካትቶ እንዲቀርብ የተቀረጸ ነው። የትምህርት-አሰጣጡ የተቀረጸው፤ ሊኖር-የሚያስፈልገውን የወላጅ ተሳትፎን ለማበረታታት፣ አዎንታዊ የሆነ የራስ-ጽንሰ-ሃሳቦችን ለማሳደግ እና ከእኩዮቻቸው-ጋር እኩል-ሆኖ ለመታየት ሲባል - የሚመጣባቸው ጫና መቋቋሚያ፣ እና እንደ ተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃዎች እና አቅሞች መሠረት - በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ የሚገጥማቸውን ጫናዎች የሚቋቋሙበትን መንገዶች ማቅረብ ነው።

የፕሮግራም ቅደም-ተከተል: በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (Virginia Department of Education) በታዘዘው-መሠረት፣ በACPS ውስጥ፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፣ ከK-10ኛ ክፍሎች - በሚከተሉትን የጽንሰ-ሃሳብ ይዘቶች ላይ በ'Standards of Learning' ላይ መሠረት አድርጎ የትምህርት-አሰጣጥን ያካትታል:

1. የቤተሰብ አኗኗር እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች፤
2. የቤተሰብ ግንኙነቶች ያላቸው ከፍተኛ-ዋጋ፤
3. የወሲባዊ-እንቅስቃሴዎችን - ወደ ሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ያለው ከፍተኛ ዋጋ፤
4. የመታቀብ ትምህርት (Abstinence education)፣
5. የሰው-ልጅ ወሲባዊ-መለያ (Human sexuality)፤
6. የሰው-ልጅ መራባት/መዋለድ (Human reproduction)፤
7. ያልታሰበ እርግዝና በሚፈጠር ጊዜ፤ ለማደን-የመስጠትን አዎንታዊ የሆነ አማራጭ - ያለው ጥቅሞች፤
8. በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች፤ መንስዔ፣ መከላከያ፣ እና የሚያመጡት ችግሮች፤
9. የሰውን-ልጅ ከቦታ-ቦታ ያለፈቃድ ዝውውር (human trafficking)ን መከላከል፤
10. የፍቅር-ጓደኝነት ጥሰት (dating violence) - በዚህ ውስጥ መካተት ያለበት፤ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ማንኛውም የወሲብ ከንውን ከማድረጋቸው በፊት ስምምነት መስጠት፣ ጥቃት-ያለባቸውን የግንኙነት ፀባዮችን ማወቅ፣ የወሲብ ጥቃትን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን፣ ሊገኙ-የሚችሉትን የማማከር እና ሕጋዊ የመረጃ-ምንጮችን ማወቅ፣ እና፣ የወሲብ-ጥቃት በሚከሰት ጊዜ - ወዲያውኑ የሕክምና ትኩረት እና ምክርን ማግኘት ጠቃሚነትን፣ እንዲሁም የሕግን አስፈላጊነት፤ እንዲያውቁ ማድረግን ያካትታል፤ እና
11. የአዕምሮ ጤና ትምህርት እና ግንዛቤ።

የስርዓተ-ትምህርት መስመሮች (Strands): ስርዓተ-ትምህርቱ፤ በአራት የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ዙሪያ የተገነባ - ይህም ጭብጥ-ያለው መስመር (thematic strands)፣ እና የሂደት መደበኛዎች - ግንዛቤዎችን ዘላቂ በማድረግ እና መሠረታዊነት ያላቸውን ሂደቶች በፕሮግራሞ መሃከል-ላይ በማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ-የተገነባ ነው።

1. ዋና ጽንሰ-ሐሳቦች (Core Concepts)
2. እራስን-መቆጣጠር (Self-management)
3. የየግል የደህንነት-ጥበቃ (Personal Safety)
4. ተፅዕኖዎችን መተንተን

ለእያንዳንዱ ክፍል - ከእነዚህ የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ጋር ጎን-ለጎን በማድረግ፤ ግቦችን ማስተላለፍ እና የከንውን-ሂደቶችን ይገመግማል።

ስርዓተ-ትምህርትን ለአንዳፍታ-በምልከታ-ላይ: በ6ኛ ክፍል የ‘FLE’ የትምህርት አሰጣጡ ወቅት፤ የሚከተሉት ርዕሶች ላይ - ምላሽ-ተሰጥቶባቸዋል።

የ6ኛ ክፍል - የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት

	ክፍል/Unit 1: **ዋና ጽንሰ-ሐሳቦች (Core Concepts)** በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - በስነ-ተዋልዶ ዘዴዎችን (reproductive systems) ውስጥ ያሉትን - ክፍሎችን እና ተግባራቶቹን የሚዳስሱበት-ይሆናል። “የግብረ-ሥጋ ግንኙነት/sexual intercourseን” ምን-ማለት እንደሆነ ትርጓሜውን የሚሰጡበት፣ እና የ‘ግብረ-ሥጋ ግንኙነት/sexual intercourse’ን ሳያከትቱ፣ ሌሎች እርግዝና-ሊከሰትባቸው የሚችሉባቸውን-መንገዶች ይማራሉ። በመጨረሻም፤ በኢኮኖሚ ልዩነቶች-መኖር/economic disparities፣ አንዳንድ-ሰዎችን እንዴት የስነ-ተዋልዶ የጤና-እንክብካቤ (reproductive healthcare)ን ከማግኘት-እንደሚያግዳቸው ይማራሉ። 1. **ትምህርት/Lesson 1፡ የመራቢያ አናቶሚ (Reproductive Anatomy) –** የወንድ እና የሴት የመራቢያ ዘዴን - የአካል ክፍሎችን እና ተግባራቸውን መለየት እና መግለጽ። 2. **ትምህርት/Lesson 2፡ የሰው-ልጅ መራባት/መዋለድ (Human Reproduction)** - እርግዝና እንዴት እንደሚከሰት፣ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት/ sexual intercourseን ሳያካትቱ - የሚከሰቱባቸውን መንገዶች ጨምሮ፤ በሰው ልጅ መራባት-ሂደት ውስጥ ምን-አይነት ሴሎች/cells እንደሚካተቱ እና እርግዝናን እንዴት መከላከል እንደሚቻል መወያየት።	**‘Standards of Learning’:** 6.6
	ክፍል/Unit 2: **እራስን-መቆጣጠር (Self-management)** በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - በ‘ጉርምስና/puberty’ ወቅት የሚከሰቱትን - አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ የማስተዋል እና ማህበራዊ/Social - ለውጦች ላይ፣ ምልከታ-ያደርጋሉ። ተማሪዎች፤ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በማድረግ የሚተላለፉ/sexually transmitted በሽታዎችን እና ኤችአይቪ/ኤድስ (HIV/AIDS)ን ጨምሮ፤ ከጋብቻ በፊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት/sexual activity ድርጊት-ውስጥ መሳተፍ - የሚያስከትለውን አደጋ ይገነዘባሉ። በመጨረሻም፤ ተማሪዎች፣ የሥርዓተ-ፆታ አመለካከቶች (gender stereotyping)ን እና ሚዲያ/media እንዴት ሚና እንደሚጫወት ይመረምራሉ። 1. **ትምህርት/Lesson 1፡ በ‘ጉርምስና/Puberty’ ወቅት-ላይ ያሉ ለውጦች** - በ‘ጉርምስና/puberty’ ወቅት የሚከሰቱትን - አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ የማስተዋል እና ማህበራዊ/Social - ለውጦችን መለየት። 2. **ትምህርት/Lesson 2፡ ስለ ‘STD’ እና ‘HIV’ መማር** -- በወሲባዊ (sexual) እንቅስቃሴ በመሳተፍ ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን፣ እና በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎችን - የመተላለፍ ስርጭታቸውን እና ያልተፈለገ-እርግዝናዎችን የመከላከያ መንገዶችን መወያየት። በተጨማሪም፣ ‘HIV’ እንዴት እንደሚተላለፍ - መወያየት። 3. **ትምህርት/Lesson 3፡ የፆታ አገላለጽ እና ስቴሪዮታይፕስ/Gender Identity and Stereotypes –** ስለ ፆታዊ-አመለካከት/sexuality እና ከስርዓተ-ፆታ አመለካከቶች/gender stereotyping ጋር የተያያዙትን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን - አዎንታዊ እና አሉታዊ መልዕክቶችን፣ መለየት እና መወያየት።	**‘Standards of Learning’:** 6.1, 6.2, 6.3, 6.4, 6.5, 6.11

<table>
<tr>
<td></td>
<td>ክፍል/Unit 3: የየግል የደህንነት-ጥበቃ (Personal Safety)

በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ የተለያዩ ዓይነት፣ ጥቃት (የሰውን-ልጅ አስገድዶ ከቦታ-ወደ ቦታ ማዘዋወር/human traffickingን ጨምሮ)፣ የጥቃት ምልከቶችን፣ እና በደንብ-ለሚያምኑት አዋቂ-ሰው ጥቃቱ እንደተፈጠረ ሪፖርት የማድረግን ጠቃሚነት፤ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ይደረጋል። በልጅ-ላይ ጥቃት መፈጸም (child abuse)ን - እንዴት ሪፖርት ማድረግ-እንደሚቻል፣ የመረጃ-ምንጮቹ (Resources) - የሚገለጹ-ይሆናል።

1. ትምህርት/Lesson 1፡ የጥቃት-ዓይነቶች (Types of Abuse) - 6ቱን ዓይነት የጥቃት-ዓይነት መለየት (አካላዊ፣ የቃላት-ትንኮሳ፣ ስሜታዊ፣ ወሲባዊ፣ ቸል-የማለት፣ እና የኤሌክትሮኒክ (Electronic)/ማህበራዊ ሚዲያ (Social Media)፤ እና እነዚህን-ጥቃቶች እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚቻል መረዳት። አስገድዶ-የሰውን ልጅ ከቦታ-ቦታ ማዘዋወር (Human trafficking)ንም በተመለከተ የሚገለጽ-ይሆናል።</td>
<td>‘Standards of Learning’:
6.8, 6.12</td>
</tr>
<tr>
<td></td>
<td>ክፍል/Unit 4: ተፅዕኖዎችን መተንተን

በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ጤናማ የሆነ ጓደኝነትን እና ስለ የግል-ጥበቃ መብቶችን (personal boundaries)ን ስለ-ማስቀመጥ፣ ተማሪዎች የሚዳስ ሱ-ይሆናል። በተጨማሪም-እምቢ የማለት ችሎታዎችን - በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ለመማር-የሚችሉበት እና ከእኩዮች ለሚደርሰው-አላስፈላጊ ግፊት (peer pressure) እንዴት-ምላሽ መስጠት እንደሚቻልም-ይማራሉ።

1. ትምህርት/Lesson 1፡ ጤናማ-የሆነ ጓደኝነቶች እና ገደብ-ማበጀት/Healthy Friendships and Boundaries – ግንኙነቶችን-በመልካም ሁኔታ እየጠበቅን እና ገደቦች/boundariesን እያስጠበቅን እያለ፤ በሃሳብ-ልዩነቶች ላይ ንግግርና ውይይት ለማድረግ፣ አዎንታዊ-የሆኑ መንገዶችን ማሳየት።
2. ትምህርት/Lesson 2፡ ከእኩዮች-ለሚመጣ ግፊት - ምላሽ-መስጠት/Responding to Peer Pressure - ከእኩዮች-የሚመጣ ግፊት (peer pressure) ምን-እንደሆነ ማወቅ፣ በግል-ባላችሁ እሴቶች/values፣ እምነቶች/values እና ግቦች/goals ላይ - ትኩረት-አድርጎ የመቆየትን-ጠቃሚነት መገንዘብ፣ እና ከእኩዮችን-የሚመጡ ጫና (peer pressure)ን የሚያካትቱ-ሁኔታዎች ላይ ምላሽ-መስጫ መንገዶችን ለይቶ-ማወቅ።</td>
<td>‘Standards of Learning’:
6.7, 6.13</td>
</tr>
<tr>
<td></td>
<td colspan="2">የ‘FLE Standards’፣ በACPS 6ኛ ክፍል የጤና ስርዓተ-ትምህርት (Health Curriculum) ውስጥ፣ ምላሽ-ተሰጥቶበታል፡
6.9, 6.10</td>
</tr>
</table>